# የሸንጎ ድምፅ

## የሸንጎ የሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ መልእክት

### ምርጫና አፈና አብረው አይሄዱም!

ዓመታቱ ዞረው መግጠማቸው የተፈጥሮ ሕግ ነውና በሃገራችን የ2002 „"የምርጫ" ግርግር አልፎ የ2007 ምርጫ ግርግር ጀምሯል። ህወሓት/ ኢሕአዴግ ዝግጅቱን የጀመረው በ2002ቱ ምርጫ ማግሥት ሲሆን፤ ተቃዋሚዎች ደግሞ የተቀላቀሉት ሰሞኑን እንደሆነ እንመለከታለን። ሸንጎ ይህንን የምርጫ ጉዳይ አስመልክቶ መጋቢት ወር 2006 ዓ. ም (ከ ዘጠኝ ወራት በፊት ማለት ነው) የመልዕክቱ ዋና ጉዳይ አድርጎ ያቀረበው ይህንኑ በ2007 ዓ. ም ይካሄዳል የተባለውን ምርጫ እንደነበር እናስታውሳለን። በዚህም መልዕክት ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን፤ በቅድሚያ መሟላት አለባቸው በማለት አስቀምጧቸው የነበረውና የምርጫው ጊዜ እየተቃረበ ባለበት ባሁኑ ጊዜም ያለው ሁኔታ እንደገና እንድንመለስባቸው የተገደድንባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ።

የምርጫ ቦርዱ ከማንም ቁጥጥር ነፃ ሆኖ በሚንቀሳቀስበት አሠራር መልክ መዋቀር እንዳለበት፣ የዜና ማሰራጫ አውታሮች ለሁሉም ተወዳዳሪዎች እኩል አገልግሎ የሚሰጡ ሆነው እንዲደራጁ፣ የፍትኅ ተቋማትና ፍርድ ቤቶች ከአገዛዙ ተጽዕኖና ቁጥጥር ውጭ በነፃነት የመሥራት መብታቸው መረጋገጥ እንደሚኖርበት፣ የጦር ኃይሉ፣ የፖሊስና የፀጥታ ክፍሉ ሥልጣን ላለው ድርጅት የፖለቲካ መሣሪያ እንዳይሆኑና በሀገር ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መመሪያ እንዲኖር ማድረግ፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች ካለምንም ገደብ በነፃነት ከቦታ ወደቦታ የመንቀሳቀስ፣ ቢሮ የመክፈት፤ የመቀስቀስ፤ ስብሰባ የማካሄድና የማደራጀት፤ መብታቸው እንዲከበር፣ በሕገ-ወጥነት የተፈረጁ ድርጅቶች ሕጋዊነታቸው እንዲረጋገጥ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ ቡድን በአገር ውስጥና ውጭ የተቃዋሚ ኅብረተሰቡን የግንኙነት መስመሮችን የመሰለል፣ የመጥለፍና የመዝጋት ተግባሩን ማቆም እንዳለበት፣ ህወሓት/ኢሕአዴግና የተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ የተስማሙባቸው አስተማማኝና ለሃቅ የቆሙ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ዜጎችን ለምርጫ ታዛቢነት መርጠው እንዲጋብዙ ማድረግ፣ ይህም አፈጻጸም ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን ማድረግና የምርጫንም ውጤት ሕጋዊነትና ሉዓላዊነት ለመቀበልና የ1997ቱን የድህረ-ምርጫ ዓይነት ኢ-ሰብዓዊና አሳፋሪ ድርጊት እንዳይፈጸም በተለይም ሥርዓቱ ዋስትና ለመስጠት ቁርጣኝነትን እንዲያሳይ አገዛዙ ማስተማመኛ መስጠት እንዳለበትና ከምርጫው ዝግጅት ተነጥሎ የማይታየውና ከምርጫው በፊት መደረግ ስለሚገባው በተለይ በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት በሰበብ አስባቡ በየእሥር ቤት የታጎሩ የድርጅት አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም የነፃው ፕሬስ አባላት ሁሉ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱ፤ ህወሓት/ኢህአዴግን በማሳሰብ፤ በተቃዋሚው ጎራም አንድነቱን አጠናክሮ በኅብረት መታገል እንደሚገባና ምርጫው በፍትሃዊነት እንዲጠናቀቅ አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደረጉ ሸንጎ ጥሪውን ማቅረቡ ይታወሳል።

በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ሕዝብን ለማደራጀት፤ ለማንቃትና ምርጫውም በንቃተ-ህሊና በተደገፈ ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ለማድረግ የሚያደርጉትን ትግልና የሚደርስባቸውን እንግልት ስናይ፤ ሥርዓቱ ለምርጫው ፍትሃዊነት የሚረዱ እርምጃዎችን ለመውሰድ ምንም ዓይነት የፍቃደኝነት ዝንባሌ የሌለው መሆኑን ነው። ስለዚህም ነው ቀደም ብለን ያቀረብናቸውን መልዕክቶች እንድንመለስባቸው የሆነው። አሁንም የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፤ ጋዜጠኞች፤ ብሎገሮች፤ ይታሠራሉ፤ ተጨባጭ መረጃ ተገኝቶባቸዋል ተብለው ከተያዙና ወደ እሥር ከተወረወሩ በኋላ፤ ለፍርድ ሳይቀርቡ ማስረጃ አልተሟላም እየተባለ የጊዜ ቀጠሮ እየተጠየቀባቸው፤ ክስ ሳይመሰረትባቸው ረጅም ወራቶች ያሳልፋሉ። ለሰላማዊ ሰልፍ የወጡ የፖለቲካ ድርጅት አመራሮችና ደጋፊዎቻቸው እንዲሁም ለሰልፍ የወጡ ሰዎች፤ ይደበደባሉ፤ ይታሰራሉ።

የቅርቡን ዘጠኝ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያቀፈው በድን "ነጻነት ለነጻ ምርጫ" በሚል መሪ መፈክር ሥር ድምጽ ለማሰማት የጠራውን የኅዳር 27 እና 28 የ24 ሰዓት የአዳር ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይደረግ ከዋዜማው ጀምሮ፤ የፌዴራሉ ፖሊስ ሳይቀር የተሳተፈበት የድብደባና የእሥር እርምጃ የ2007ን ምርጫ ጥቁር ዳመና ያንጃበበት መሆኑን ማሳያ ምልክት ነው ብሎ ለማለፍ የሚያስችለን ምንም መተማመኛ ከማጣታችንም አልፎ፤ ለድብደባና ለእሥር ከተዳረጉት ውስጥ በተለይ የየድርጅቶቹ አባላት ከእሥሩ ቢለቀቁም፤ ምክንያት እየተፈለገ ከሥራ ገበታቸው የሚፈናቀሉትን ጨምረን ስናይ፤ የ2007 ምርጫን ፍትሃዊ ለማድረግም ሆነ፤ ባጠቃላይም በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል የሚጠይቀውን ዋጋ ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ ነው።

ስለሆነም ሥርዓቱ ሕብረተሰቡን በሽብር በማሸማቀቅ አሁንም ምርጫውን በራሱ ቁመና ለክቶ ለመስፋት የሚያደርገውን ጥረት ለመቋቋም በሀገር ውስጥ ተደራጅታችሁ የምትንቀሳቀሱ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሁሉ ለአንድና ለወሳኝ ጥያቄ ማለትም በዚያች ምድር ላይ "ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ" ተካሂዶ ለማየት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በማተኮር፤ ትግላችሁን እንድታቀናጁ እያሳሰብን እኛም ከጎናችሁ የቆምን መሆናችንን እናረጋግጣለን። ሥርዓቱም ቀኑ ሳይመሽ የሕዝብን ጥያቄ አዳምጦ ከሕሊናው ጋር ታርቆ ምርጫና አፈና አብረው የማይሄዱና በሁለቱ መካከል በሚፈጠር ግጭት ማንም አትራፊ እንደማይሆን ተገንዝቦ፤ ምርጫው ፍትሃዊ እንዲሆን የሚጠበቅበትን ሃላፊነት እንዲወጣ ሸንጎ ያሳስባል።

# ዜናዎች

## አንድነትና መኢአድ ለኢትዮጵያ አንድነትና ክብር የቆሙ ናቸው ሲል ሸንጎ ገለጸ

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) አንድነትንና መኢአድ ብሄራዊ አጀንዳ ያላቸውና ለሀገሪቱ ሉአላዊነት ክብርና ነጻነት የቆሙ ናቸው ሲል ድጋፉን ገለጠ፤ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድን አወገዘ።**

የኢትዮጵያ መንግስት የዚህን ዓመት ብሄራዊ ምርጫ በብቸኝነት ለመቀጠል እንዲያስችለው ብሄራዊ አጀንዳ ያላቸውንና በብርቱ ይፈታተኑኛል ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ሰበብ በመፍጠር ከምርጫ አግዷል።

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በአንድነትና በመኢአድ ድርጅቶች ላይ የወሰደው የመከፋፈልና የማገድ ተግባር፣ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በአለማቀፍ ሰብአዊ መብት ተቆርቋሪዎች ዘንድ ውግዘትን አስከተለ። ይህንኑ ድርጊት ካወገዙት መካከል ሸንጎ አንዱ ሲሆን ስለዚሁ ጉዳይ “ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ንቅናቄን አያቆመውም” በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ፣ የምርጫ ቦርዱን ሲያወግዝ በተቃራኒው ለሁለቱ ድርጅቶች ያለውን ድጋፍ አረጋግጧል።ሸንጎው በዚሁ መግለጫው አንድነትና መኢአድ እና ሌሎችም ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት፣ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለዘላቂ ሰላም የቆሙ ሲል አድናቆቱን ገልጧል። ሸንጎው በመጨመርም በሕግ የበላይነትና ለዘላቂና ፍታዊ እድገት መኖር የጸና እምነት ያላቸው ለዚሁም መስዋእት መሆን የወሰኑ ታጋዮችን መደብደብ፣ አካለ ስንኩል ማድረግ፣ እርጉዝ መርገጥ፣ አዛውንቶችን ሳይቀር በግፍ አግዟል በማለት አገዛዙ የሚያደርገውን በደል አስፍሯል። ሙሉ *[መግለጫውን ከዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ።]*

በሌላ በኩል ደግሞ የህወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለማንበርከክ በአንድ ማእከል የሚንቀሳቀስ አማራጭ ኃይል ማቋቋም ወቅታዊ ነው ሲሉ ሸንጎና የሽግግር ምክር ቤት ጥር 20 ቀን 2007 ባወጡት የጋራ መግለጫ አስታወቁ፡;

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት በዚሁ የጋራ መግለጫቸው ላይ የህወሓት/ኢህአዴግ የግፍ አገዛዝ እያደረሰ ያለውን ጥፋት ከዘረዘሩ በኋላ ለዴሞክራሲ የቆሙ ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች በተበታተነ መልክ የሚያደርጉት ትግል በያቅጣጫው እያፋፋሙ እንደሚገኙ በማረጋገጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባላት አለኝ በማለት ከውነት የራቀ ፕሮፓጋንዳ ሲነዛ የከረመው መንግስት በአባላቶቹ ላይ እምነት በማጣትና በብሄራዊ ደረጃ የተደራጁትን ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች በመፍራት በአዋጅ የማጥፋት ተግባር መፈጸሙ አሳፋሪ ነው ብለዋል።

ሁለቱም ድርጅቶች በዚሁ የጋራ መግለጫቸው በምርጫ ቦርድ አማካኝነት አንድነትና መኢአድ ሊያደርጉት የነበረውን ውህደት ማገዱን አውስተው አሁን ደግሞ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል በውስጣቸው እንዲከፋፈሉ በማድረግ አንዱን ህጋዊ ሌላውን ህገወጥ በማለት የማፈረስ ተልኮ በግልጽ መፈጸሙን አብራርተዋል። የሁለቱ ድርጅቶች ምግለጫ በርካታ ጉዳዮችን ከዘረዘረ በኋላ ሕዝባዊ ትግሉን የሚያስተባብርና አቅጣጫ የሚያስይዝ አማራጭ ኃይል መፍጠርና መታገል ወደሚጠይቅበት ምእራፍ መሸጋገር አስፈላጊ ነው ብሏል። መግልጫው በመጨረሻም ኢትዮጵያ አንድነቷንና ሉአላዊነቷ ተከብሮ፣ የዜጎች መብት ተጠብቆ፣ የህግ የበላይነት እውን የሆነበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማስፈን ተፈቃቅዶና ተከባብሮ መስራት አማራጭ የለሽ ጉዳይ ነው ብሏል።

ሁለቱ ድርጅቶች አብሮ ለመስራት በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ ያለውን ትብብር በይበልጥ መስመር ለማስያዝና ወደ ከፍተኛ እርከን ለማሸጋገር በድርጅቶቹ ከፍተኛ አመራሮች ደርጃ ምክክር በማድረግ ላይ መሆኑን በማሳወቅ በየካቲት ወር መጨረሻ የጋራ ሕዝባዊ ስብሰባ ለመጥራት ውሳኔ ላይ መድረሳቸውን አስታወቀዋል።

## የምርጫ ቦርድ ውሳኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ተቀባይነት የለውም ሲል አንድነት አስታወቀ

አንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ ከዘንድሮው ምርጫ በታገዱንና የድርጅቱን አመራር ለህወሃት ታማኞች ተቀመቶ መስጠቱን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ ”የገዢውን ፓርቲና መንግስትን ሸፍጠኝነት ያጋለጠው የምርጫ ቦርድ ውሳኔ በሕዝቡ ዝንድ ተቀባይነት አይኖረውም” ሲል አስታወቀ።

ፓርቲው በዚሁ መግለጫው የጥር 21 ቀን 2007 ዓ.ም የምርጫ ቦርድ ውሳኔ ድርጅቱ ያለበትን የዘቀጠ ደረጃ ይፋ ያደረገ ነው ያለው አንድነት ቦርዱ በዚህ ደረጃ እንዲዋረድ ከጀርባ ሁኖ አመራር የሚሰጡት ገዛው ፓርቲና መንግሰትም የውርደት ደረጃ ለኬታቸውን አስመስክረዋል ብሏል። የፓረቲውን መግልጫ ይህን በመጫን ማንበብ ይቻላል።

በተመሳሳይ ዜና አዲስ አባባ የሚገኘው የየካ ፖሊስ ጣቢያ የአንድነትን ቢሮ ውሮ ድርጅቱን መዝረፉንና ምርጫ ቦርድ ይታዘዙኛል ላላቸው ለእነአቶ በውነቱ አወል ጽፈት ቤቱን መስጠቱ ታውቋል።

## በደቡብ አፍሪካ ስደተኞች እየተገደሉና እየተዘረፉ ነው

አለማቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ በደቡብ አፍሪካ በሚገኙ የሶስት ሃገራት ስደተኞች ላይ በሀገሬው ሕዝብ ለጥቃት መዳርጋቸው በእጅጉ እንዳሳሰበው ገለጸ።

የሰደተኞች ተከታታይ ድርጅት ቃል አቀባይ የሆኑት ጀየል ሚልማል እንደሚሉት ባለፉት ሁለት ሳምንታት ብቻ በሲዌቶ፣ በጁሃንስበርግ፣ በአሌክሳደሪያ፣ በላግሌትና በአካባቢው ከተሞች በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በባንግላዲሽ ዜጎች ላይ በርካታ ጥቃቶች መድርሳቸውን አስታውቀዋል።

በቃል አቀባዩ መግለጫ መሰረት በዚሁ ጥቃት ዘጠኝ ስደተኞች

ተገድለዋል። 700 የሚሆኑ በዘረፋ ሙከራ ወቅትና በቀጥተኛ ጥቃት ያካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን፣ በመግለጽ በነዚህ የመግደልና የማቁሰል ብሎም በዘረፋ የተጠረጠሩ 165 ደቡብ አፍሪካዊያን በእስር ላይ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

የጥቃቱ ምክንያት ነው የተባለው በርካታ ስደተኞች የደቡብ አፍሪካን ስራ ተሻምተዋል፣ እንደዚሁም በሀገሪቱ የማህበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል የሚል ምክንያት እንደሚያቀርቡ የገለጹት ቃል አቀባዩ፣ በተቃራኒው በርካታ ስደተኞች ለሀገረቱ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚውል ስራ መፍጠራቸውን በማብራራት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

በደቡብ አፍሪካ ተመዝግበው የሚገኙ ስደተኞች 1.6 እስከ 2 ሚሊዮን እንደሚደርሱ የሚገመት ሲሆን፣ በሕገ ወጥ ይኖራሉ ተብለው የሚገመቱ ደግሞ፣ ከአምሰት እጥፍ በላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል ብለዋል።

# መጣጥፎች

## አጥፍቶ በመጥፋት ፈጣን ጉዞ ላይ ከሚገኘው ስርዓት እንዴት እንታደግ?

የኢትዮጵያ ህዝብ በገዥዎቹ እየደረሰበት ያለውን የመሰረታዊ መብት መጣስና ግፍ ለሚሰማ ወይንም ለሚመለከት ፍጡር በእውነት ይህ ግፍ የሚካሄደው ጤነኛ አእምሮ ባላቸው በራሳቸው አገር ዜጎች ነው? ብሎ እሰከ መጠራጠር ቢደርስ አያሰገርምም። በብዙ ሀገሮች በአመታት ውስጥ አንድ ቀን ቢከሰቱ የህዝብን ቁጣ የሚቀሰቅሱ አሳፋሪ ምግባሮች ለምሳሌም ያለፍርድቤት ትእዛዝ የአንድ ዜጋ ተጎትቶ መታሰርና በፖሊስ መደብደብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረገን ህዝብ በጥይት መቁላት፣ የሰውን ንብረት እንደፈለጉ መንጠቅ፣ ሰውን ከስራው በፖለቲካ አመለካከቱ የተነሳ ማባረር፣ ከመኖሪያ ቦታው በሚናገረው ቋንቋ ምክንያት ማባረር ....ወዘተ እጅግ አሰቃቂ ተብለው ከሚመደቡ ግፎች ውስጥ የመሚመደብ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ደግሞ በየእለቱ የሚደርስበት በደል ነ።

ለ23 አመታት የተካሄደውን ማለቂያ የሌለው አሰከፊ ግፍ ባብዛኛው ወደጎን ትተን ላለፉት ሁለት አመታት ከተካሄዱት ውሸጥ ጥቂቶቹን ብቻ ብንመለከት እንኳ፣ ፊትለፊት የሚገጥመን ዘግናኙ ግፍ እንቅልፍ የሚነሳ ነው። የሚከተሉትን እናንሳ፡-

- በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቤነሻንጉል በሚናገሩት ቋንቋ ምክንያት ብቻ ለዘመናት ከኖሩበት ቀየ ንብረታቸውን ተነጥቀው በመንግስት ባለስላጣናት እቅድና አበረታችነት አነዲባረሩ የተደረገው ባሳለፍነው አመት ጭምር ነው፣
- በመንግስት የጸጥታ ሀይሎች በኦጋዴን የሚካሄደው አስከፊ ጭፍጨፋ እንደቀጠለ ነው፣
- ከጥቂት ወራት በፊት የአምቦ የነቀምቴ የጂማ ፣ የአሶሳ ተማሪዎችና የአካባቢው ባለስልጣናት "የልማት " እቅድ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ የወጡ ወገኖቻችን የመንግስት የጸጥታ ሀይሎች በጥይት ደብድበው ብዙዎችን ገድለዋል ፣ በርካቶችን አቁስለዋል ሌሎችን ደግሞ ለእስር ዳርገዋል፣
- ከጥቂት ሳምንታት በፊት በባህዳ ዳር ከተማ ሰላማዊ ሰላፍ በማካሄድ ያካባቢው ባለስልጣናትን ሊያፈርሱት ያሰቡትን የሀይማኖት አደባባይ የለም መፍረስ የለበትም በማለት ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ የወጣውን ህዝብ በጥይት ደብድበው ገድለዋል አቁስለዋል፣
- ከባህር ዳሩ ጭፍጨፋ አንድ ሳምነት ቀደም ብሎ ደግሞ ባዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡትን የዘጠኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች ስብስብ አባላትና ደጋፊዎችን ገና ከመነሻቸው በዱላ በመቀጥቀጥ አሰቃይተዋል ብዙዎችን ለእስር ዳርገዋል፣
- በዚያኑ ሰሞን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያንድነትንና የመድረክን አባላት የመንግስት ወታደሮች ሲደበድቡና፣ ሲያሰሩ ነው የከረሙት፣
- በፖለቲካ ድርጅት መሪዎች በእነ ሃብታሙ አያሌውና፣ አብርሀ ደስታ ላይ የተለመደና የሰለቸ የፈጠራ ክስ መስርቶ ወደ እስር የተወረወሩት በዚህ ባለፈው አመት ውስጥ ነው። እነዚህ ታሳሪዎች በጨለማ ቤት ታስረው እንደተደበደቡ፣ ሰቃይ እንደደረሰባቸው፣ ንብረታቸው እንደተዘረፈ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሳይፈሩ እየተናገሩ ነው፣
- በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ ያነጣጠረው እስራት፣ ድብደባ ፣ ማዋከብ እነሆ ከሁለት አመት በላይ አስቆጠረ፣
- የነጻውን ፐረስ አባላት ከምን ጊዜውም በላይ መፈናፈኛ በመንሳት በእስር የሚቅቁት ቁጥር አስራ ሰባት የደረሰውም በዚሁ ዓመት ውስጥ ነው፣
- ስርአቱ ዛሬ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የሚደርሰባቸውን ግፍ ችለው በሰላም በመታገል ላይ የሚገኙትን አንድነትን፣ መኢአድንና ሰማያዊንና መድረክን ገፍትሮ ለማሰወጣትና ለብቻው መፏለሉን ለመቀጠል ግፊቱን አጠናክሮታል፡

ይህ ሁሉ ግፍ በገሀድ በሚካሄድባት ኢትዮጵያ ውስጥ የስርአቱ መሪዎችና አጫፋሪዎቻቸው ደግሞ ምንም እንዳላተካሄደ፣ እንዲያውም በተቃራኒው ሀገራችን ሰላም በሰላም እንደሆነች ህዝቡም በደስታና፣ በዴሞክራሲ ተምበሽብሾ ጮቤ እየረገጠ እንደሆነ፣ ከዚያም አልፎ ገዝዎቹ ላጎናጸፉት መብት አድናቆቱን በእልልታና ጭፈራ እየገለጸ እንደሆነ ሊያሳምኑን ሌት ተቀን ይጥራሉ።

በህዝቡ ላይ የሚካሄደውን አስከፊ ጭቆና ባንድ በኩል እና ስርአቱ

የሚገኝበትን የክህደት አለም በሌላ በኩል ለሚያነጻጽር ሰው ሀገራችን ስልጣን ላይ ያሉት መሪዎች ምንድነው የሚያደርጉት? በእውነት ጤነኞች ናቸው? በዚህ ከቀጠለስ የሀገራችንና የህዝባችን እጣ ፈንታ ምን ይሆናል? ብሎ እንዲጨነቅና እንዲጠበብ ይገደዳል።
ሀገራችን በየእለቱ በፍጥነት ከድጡ ወደማጡ እያሽቆለቆለች ነው። የስርአቱ መሪወች ደግሞ የያዙትን ስልጣን ከመንከባከብ ውጭ ካጥፊ ጉዟቸው ወጥተው ሀገርንና ህዝብን ከጥፋት ለማዳን (ራሳቸውንም ለማዳን) ምንም ለማሰብ አልቻሉም። የስርአቱ ጉዞ ሀገራችንን እጅግ አደገኛ ወደሆነ ሁኔታ ባጣዳፊ ፍጥነት እየገፈተራት ነው፡፡
በስርአቱ ግፍ የተማረረው ህዝብ ቁጥር እጅግ በዝቷል። በዚህ ስርአት ስር ምንም አይነት ጥሩ ነገር ይገኛል የሚለው ተስፋው የተሟጣጠው ህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው። ትላንት ይህን ስርአት በወዳጅነት ይመለከቱ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ዛሬ ምርር ብሏቸዋል። አዲሱ ትውልድ በዚህ ስርዓት ስር ምንም ተስፋ እንደሌለው ስለተገነዘበ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ መሰደድን መርጧል። በዚህ ስርአት ስር መኖር እጅግ መሯቸው እነሆ እየተደበደቡ፣ እየተዋረዱ፣ እየተደፈሩ በሚኖሩባቸው ባእድ ሀገሮች ለመኖር እህቶቻችን እየተገደዱ ነው።
ካገዛዙ የ23 አመት ባዶ ጩኸት በኋላ ዛሬም በርሀብ የሚቆሉት፣ ኑሮን መቋቋም ያልቻሉት ከቆሻሻ መጣያ ቦታ በሚገኝ ምግብ ህይወታቸውን ለማቆይት የተገደዱት ብዙ ኢትዮጵያውያን ናቸው።
ትላንት በብዙ አኩሪ ጉዳዮች ታዋቂ የነበረችው ሀገራችን በዚህ ስርአት ውስጥ ደግሞ በተለያዩ አሳዛኛና አሳፋሪ ጉዳዮች ቁንጮ እየሆነነች ነው። ባለፈው ወር የወጣ የአሜሪካ መንግስት ሪፖርት ኢትዮጵያን የሴተኛ አዳሪነትና ሰውን አደገኛ በሆነ ሁኔታ በህገወጥ መንገድ በማዘዋወር ቀንደኛ ከሆኑት ሀገሮች ውስጥ መድቧታል።
ይህ ሁሉ የህዝባችን አኩሪ ማህበራዊ እሴቶች እየተቦረቦሩ፣ የሀገሪቱ ህልውና አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ስርአቱም ቢሆን ሊቆጣጠረው ከሚችለው ውጭ እጁ ላይ የሚፈነዳ ቦምብ ተሸክሞ እንደሚጓዝ ያሳያል።
የገዥዎቻችን አያያዝ ለሀገርም ለህዝብም የማይበጅ ነውና ባስቸኳይ እንዲቆም ሁላችንም ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይገባናል። ተቃዋሚዎች ህዝብን በማስተባበር፣ ይህ አስከፊ የግፍ ስርአት ባስቸኳይ ወደ መጨረሻው ግብአት እንዲደርስ ማድረግ ይገባቸዋል።
በስርአቱ ደጋፊነት የተሰለፉ ሁሉ ይህ ስርአት የሚያደርሰውን ግፍ ከራሳቸው ቅንጦት አኳያ ብቻ ሳይሆን ከተጎዱት ፣ ተሰፈ ከቆረጡት፣ አባት እናቶቻቸውን ካጡት ግለሰቦች አንጻር በመመልከት ይህ ግፍ ምን ያህል ህዝባችንን እንደጎዳ እንዲመረምሩት ያስፈልጋል።

አሁንም ስርአቱን ለሚደግፉ ሁሉ ይህን እላለሁ - እስኪ ላንድአፍታ በባህር ዳር ሰልፍ ላይ የተገደሉት ሰዋች ወንድምና እህቶቻችሁ አድርጋችሁ ራሳችሁን ተመልከቱ። የህይማኖት ቦታው ለነጋዴ መሸጡን በመቃወም በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን ለማሰማት ሰለወጣ ብቻ ወንድማችሁ በመንግስት ወታደር በጥይት ተደብድቦ ሞተ ተብሎ ሲነገራችሁ ምን ይሰማችኋል? ልባችሁ ይሰበር ይሆን?
እስኪ ደግሞ ለጥቂት ደቂቃ የሰላም ታጋዩ የአንዱአለም አራጌ ወይም የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ወንድም እንደሆናችሁ ራሳችሁን ገምቱ።
አንዱአለምም አስክንድርም የፍቅር እንጂ የጥላቻ ሰወች አይደሉም ። በእምነታቸው ምክንያት በሀሰት ክስ እድሜ ልክ ተፈርዶባቸው ከህጻን ልጆቻቸው እና ከሚወዷቸው ሚስቶቻቸው ተለይተው በእስር እየተሰቃዩ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ታዲያ በያንዳንዳችሁ ቤተሰብ ላይ ቢደርስ ምን ይሰማችኋል?
እና እያንዳንዱን የስርአቱ ባለሟልና ደጋፊዎች፣ ራሳችሁን በዚህ መልክ እንድትመረምሩ እጋብዛለሁ። ይህ ግፍ እንዲቀጥል መፈቀድ አለበት ትላላችሁ? በዚህ መልክ እየተካሄደ ያለውን የቤተሰብን መለያየት፣ የህጻናትን ከቤተሰቦቻቸው መነጠል እና መሰቃየት፣ ማስቀም ተገቢ አይደለምን? ሰወችን መደብደብ መግደል ፣ በግፍ ማሰርና ማሰቃየት ፣መቆም የለበትም?
ለዚህ ሁሉ ታዲያ የግፍ ተባባሪ ሳይሆን የምፍትሄ ፍለጋው አካል ለመሆን ምን ማድረግ ይኖርባችኋል። ይህ ጉዳይ ሊታሰብበት የሚገባ ፣ አጣዳፊ ምላሽንም የሚሻ ነው። ከህሊና ወቀሳ እና ከወደፊትም ተጠያቂነት ለመዳን የሚያስችለው እርምጃ የሚገኘው በያንዳንዱ ሰው እጅ ውስጥ ነው ።
ፍትህና የህግ የበላይነት ባልሰፈነበት ህብተሰብ የማንም ጥቅም በቋሚነት አይጠበቅም። ትላንት የበላይ የነበሩት ዛሬ ወደ ትቢያ እንደተወረወሩ ሁሉ አሁንም በተመሳሳይ መስክ የተሰማሩ ሁሉ ተመሳሳይ ጽዋ እንደሚደርስባቸው በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል። ጥያቄው ያ ቀን መቼ ነው የሚሆነው የሚለው ብቻ ነው።

ዛሬ ጥያቄው በአጥፍቶ መጥፈት ጎዳና በፍትነት እየተጓዘ የሚገኘው ስርአት በሀገርም በህዝብም ላይ ይበልጥ ጥፋት ሳያስከትል እንዴት እንታደግ ነው፡፡ ይህ አዙሪት እንዲሰበር ደግሞ ሁላችንም የለውጡ አካል ልንሆን ይገባል፡ ይህ ጉዳይ ነገ ሳይሆን ዛሬ ተግባራዊ መልስ ያስፈልገዋል።

ኑ የህዝብ ወገን ሁኑ። ኑ የግፍ ስርአት በቃ በሉ፡ ኑ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስቃይ የኔም ስቃይ ነው በሉ። ለጋራ ሀገርና፣ ለጋራ መብት በጋራ እንነሳ።

## መጭው ምርጫና የተቃዋሚው ጎራ

በኢትዮጵያ ውስጥ ሕጋዊ እውቅና አግኝተው የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ተሰልፈናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና በክልል ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም። ጎን ለጎንም ሕጋዊነት ሳይኖራቸው በየጎረቤት አገሩ የተለያዩ ባንዲራ ተሸክመው በልዩ ልዩ የነጻነት ግንባር ስም ወታደራዊ አመጽ ለማካሄድ የተሰለፉ ሃይሎች እንዲሁ ቁጥራቸው የበዛ ነው። እነዚህ የተለያዩ ድርጅቶች በያዙት መንገድ ከቀጠሉ በአንድነት ግንባር ስር ለእውነተኛ ዴሞክራሲና አገራዊ አንድነት ለመታገል የሚያስችለውን ጎዳና እያጠበበውና አስቸጋሪ እያደረገው ይሄዳል። የአንድነት ግንባር ሳይኖር ደግሞ የጋራ ጠላትን አሸንፎ ላለሙት ግብ መብቃት አይቻልም። በአንድ ግንባር ስር ላለመታገል ምክንያት የሆነው አንዳንዶቹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አጀንዳ ባለማያዛቸውና ለከባቢ ጠባብ ዓላማ መሰለፋቸው ነው።ሁሉም የሚሻውና የሚጠብቀው በአገሪቱ ውስጥ አለመረጋጋት ተፈጥሮ የድርሻውን ቦጭቆ የከባቢ መንግስት ለማቋቋም ነው። ይህ አቋም ደግሞ

በስልጣን ላይ ካለው የኢሕአዴግ ቡድን የተለዩ አይደለም። ልዩነታቸው አንዱ በስልጣን ላይ መቀመጡና ሌላው የስልጣኑ ተካፋይ አለመሆኑ ብቻ ነው። የመጨረሻው ግባቸው አንድ ነው፤ኢትዮጵያን አፈራርሶ ደቃቃ የክልል መንግስታትን ማቋቋም መሆኑን የሚጠሩበት ስም፣ የትግራይ ነጻነት፣ የቤኒሻንጉል ነጻነት፣ የጋምቤላ ነጻነት፣ የኦሮሞ ነጻነት፣ የአፋር ነጻነት፣ የሲዳማ ነጻነት፣ የአፋር ነጻነት፣ የኦጋዴን ነጻነት... ያረጋግጣል።

በአገር አቀፍ ዓላማ የተሰለፉትም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁ የድርጅት ስልጣን ፍቅር አባዜ ውስጥ ገብተው ለመገንጠል ከሚሹት ቡድኖች ያላነሰ በደል በትግሉ፣ በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ ፈጽመዋል አሁንም እየፈጸሙ ይገኛሉ። ይህ በተደጋጋሚ የታዬ የተቃዋሚው ጎራ ድክመት አሁንም ሳይፈታ ባለበት ቀርቷል። ላለው ስርዓት የስልጣን ዕድሜ መራዘም የህወሃት/ኢሕአዴግ አርቆ አሳቢነትና ሕዝባዊነት በመሆን የመጣ ሳይሆን የተቃዋሚው ጎራ እንደ አማራጭ ሆኖ ፈርጠም ብሎ ለመቆም አለመቻሉ፣ እርስ በርሱ መጠላለፉ፣ መድከሙና መዝረክረኩ ብሎም ብሶቱ ጣራ የደረሰውን ሕዝብ መርቶ ለሚፈልገው ስር ነቀል ለውጥ ለማብቃት አለመቻሉ ነው። ወደፊትም በዚሁ ያለመተባበር ባህል ከተቀጠለ በማንኛውም የትግል ሜዳ ቢሰማሩ ውጤቱ ዜሮ ሆኖ ይቀራል። በዚህ ምስቅልቅል ሁኔታ ላይ ሆኖ ገዥው መንግስት በየአምስት ዓመቱ በሚያካሂደው ምርጫ ተሳትፎ ለውጥ አመጣለሁ ማለት ዘበት ነው። እንኳንስ በአሁኑ ሁኔታ ማለትም ኢሕአዴግ በብዙ መልኩ ክንዱን ባጠነከረበት ቀርቶ በዝረራ የተሸነፈበት የ97ቱ የምርጫ ውጤት እንኳ ከአረመኔያዊ ጭፍጨፋና አምባገነናዊ ከሆነ እርምጃ አላገደውም።ለዛም ያበቃው ምርጫውን ተከትሎ በተቃዋሚው ጎራ የተፈጠረው መፍረክረክ ነበር። ከዛም ቀጥሎ በ2002 ዓ.ም በተደረገው ሁሉንም ተቃዋሚውን ያላካተተ የዝግ ምርጫ ውጤቱ ያሳዘነም ያስገረመም ደጋፊዎቹንም ያሳፈረ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እራሱ መራጭ እራሱ ተመራጭ እራሱ አስመራጭ እራሱ ቆጣሪ እራሱ አስቆጣሪና መስካሪ ሆኖ የተጫወተው ምርጫን ትርጉመቢስና ቀልድ ያደረገው ድራማ ነበር።

አሁንስ ከዚያ የተለዬ ሁኔታ አለወይ?መልሱ የለም ነው። አሁንም ሁሉን ነገር በመቆጣጠር ለተቃዋሚው መፈናፈኛ የሚሆን የነጻ መድረክ አልተከፈተም፤አፈናው ከቀን ወደቀን እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።በተቃዋሚውም በኩል እርስ በራሱ እየተጠላለፈ አንድነት ግንባር ሊመሰርት አልቻለም፤ እንኳንስ አንዱ ከሌላው ጋር ሊተባበር ቀርቶ በአንድ ድርጅት አባላት ውስጥ ሰላምና አንድነት የለም።የስልጣን ሽኩቻው እንደቀጠለ ነው። ከድርጅት አፈንግጦ ለኢሕአዴግ መሳሪያ ለመሆን እጁን ለመስጠት የሚግደረደርም አልጠፋም። በየድርጅቱ ለጥቅም የተገዛው ሰርጎ ገብ ተሰማርቶ በየቀኑ የሚፈጥረው ግርግር ሕዝቡ በድርጅቶች ላይ እምነት እንዳይኖረው አድርጓል።

እርስ በራሱ እየተጠላለፈ ቀርቶ አንድ ላይም ሆኖ የህወሃት/ኢሕአዴግን ተንኮል ለመናድ አይቻልም ባይባልም አድካሚና አዳጋች ያደርገዋል።ለምርጫ የሚያስፈልገው ቅድመ ሁኔታ ባልተሟላበት ሜዳ ላይ ተሰልፎ አሸንፋለሁ ማለት ህልም ሳይሆን ቅዠት ነው። የምርጫ ቦርዱን፣ የምርጫ ሳጥኑን፣ ድምጽ ቆጣሪውን ከመቆጣጠሩም በላይ መራጩን ሕዝብም በማሸበርና በጊዜያዊ ጥቅም በመተብተብ ደጋፊና የድርጅቱ አባል ለማድረግ ያልገለበጠው ድንጋይ የለም። በመዳፉ ስር ያለውን ቀርቶ በውጭ አገርም የሚኖረውን በድክመቱ ማለትም በቤት ስራና በመሬት መቀራመቱ ዘመቻ ላይ ተሰልፎ የስርዓቱ ደጋፊ ለማድረግ ያደረገው ጥረት ከሞላ ጎደል የተሳካለት ይመስላል።ጥቂት የማይባል በስደት አገሩን ለቆ የወጣው ዜጋ በዚሁ የቅርጫ ግብግብ ተሰልፎ ገንዘብና ጉልበቱን ጊዜውን ጭምር እያባከነ ነው።ከድሃውና ከነባሩ እየተነጠቀ የሚሸጥለትን መሬት እንደበጎ ስጦታ በመቁጠር በሞቶ ሽህ የሚቆጠሩ ወገኖቹን ማደሪያ ቢስ አድርጓቸዋል። ጥቅሜ ይነካብኛል በሚል ስጋትና ፍርሃት ኢሰብአዊ ድርጊት ሲፈጸም፣ አገር ሲበዘበዝና ሲቸበቸብ አይቶ እንዳላዬና ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆን የዝምታ ድጋፉን በመለገስ ላይ ነው።አልፎ ተርፎም ያለው ስርዓት ለሚያራምደው አፈና በልዩ ልዩ ልማት ስም ለሚሰበስበው የገንዘብ መዋጮ ጥሪ አዳራሽ ሞልቶ ሲራኮት ይታያል።ለሰብአዊ መብትና ለአገራዊ ጥቅም፣ለሰላምና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ጥሪ ግን የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሎ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ በሩን ዘግቶ ይቀመጣል።በራስ ወዳድነት ሰንሰለት ተተብትቧል። አገርና ሰላም ሳይኖር ሃብትና ንብረት ማግበስበሱ ዋጋ እንደማይኖረው፣ በሰላም ውሎ ማደር እንደማይቻልም የተገነዘበው አይመስልም። ይህንንም በኢራቅ፣በሊቢያ፣ በሶሪያና በቀሩትም አገሮች የሆነውንና የሚሆነውን እያዩ ሊማር አልቻለም።

ሕወሃት/ኢሕአዴግ የ97ቱን ክፍተትና ያደረሰውን ኪሳራ ዳግም ላለማየት ቀዳዳዎቹን ሁሉ ደፍኗል። የጦር ሃይሉ፣የፖሊስና የጸጥታው፣ የዜና ማሰራጫው፣ የአገሪቱ የገንዘብ ምንጭና ካዝና ሳይቀሩ የሱና ለሱ የሚሰሩ ተቋማት ናቸው።በዚህ የምርጫ ምህዳሩን አጥብቦ ተቆጣጥሮታል። የሚያደርገው ዝግጅት፣የሚያወጣው ህግና መመሪያ የዘጠና ሰባቱ ስህተት እንዳይደገምና ስልጣኑ ከእጁ እንዳይወጣ ለማድረግ ነው። ምናልባት በዘንድሮው ምርጫ እንዳለፈው ጊዜ አይን ያወጣ የምርጫ ውጤት ላይደግም ይችል ይሆናል። ደጋፊዎቹን ላለማስቀየምና ላለማሳፈር ሲል ምናልባት አደገኛ ናቸው ብሎ ለማይገምታቸው ለስሙ በተቃዋሚ ስም ለተመዘገቡ በተለይም ለጎሳ ተኮር ድርጅቶች በሩን ገርበብ ሊያደርግላቸውና ጥቂት ወንበሮች ሊለቅላቸው ይችል ይሆናል። ይህ ግን ምርጫውንና ሂደቱን ዴሞክራሲያዊ ያደርገዋል ማለት አይደለም። የወንጀል ስራውንና አምባገነንነቱን የሚሸፍንበት ካባ ከመሆን አያልፍም።

ለተቃዋሚ ጎራ በተለይም ለአንድነት ሃይሉ ያለው ምርጫ አንድ ነው፤ ይህም በአለው አጣብቂኝ ውስጥ ለምርጫ መሯሯጡ ሳይሆን መራጩን ሕዝብ ማደራጀትና ሕዝባዊ አድማና እምቢ ባይነት እንዲቀጣጠል ማድረግ ነው።ምርጫው ባለው መንግስት ሳይሆን ሁሉን ባካተተ ብሔራዊ የሽግግር መንግስት እንዲካሄድ፣ የምርጫ ሕጎች እንዲከበሩ፣ የጦር ሃይሉና የፖሊሱ ተቋም ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት አገልጋይነት ተላቀው ለአገራዊ ጥቅም እንዲቆሙ መታገል ነው። ይህንን ለማድረግ ደፍሮ መነሳት፣ አደባባይ መውጣት ያስፈልጋል፤ በመግለጫና በስብሰባ ማውገዝ ብቻ በቂ አይደለም። እርግጥ ነው የህወሃት/ኢሕአዴግ ምላሽ ቀላል አይሆንም፤ ግን የማታ ማታ ድሉ የሕዝቡና የተቃዋሚው ጎራ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ትግሉ እየጎላ ሕዝብ ደፍሮ በአደባባይ ሲወጣ ኢሕአዴግን እሹሩሩ እያሉ ተባባሪ የሆኑትም የውጭ አገር

መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች “አይተነው ጊዜ”በሚለው የመገለባበጥ ጸባያቸው ሳይወዱ ፊታቸውን ወደተቃዋሚው ጎራ ማዞራቸው አይቀርም። ይህ ይሆናል ተብሎ ግን እነሱን መተማመንና የነሱን ቡራኬ ማሳደድ የድክመትና የባርነት ምልክት ስለሆነ የተቃዋሚው ጎራ በራሱና በሕዝቡ ብቻ መተማመን ይኖርበታል።እራሱን ካከበረ ይከበራል;ለጥቅምና ለድጋፍ ብሎ በየኤምባሲው ደጃፍ መደርደርና መራኮት እራሱንና ሕዝቡን ማዋረድ ይሆናል። የአገርንም ልዑላዊነት ይጻረራል። ይህ በተደጋጋሚ በአገራችንና በሌሎቹ አገሮች የታዩ ክስተት ነው። በአሁኑ ጊዜ ተቃውሞው ገና ባልጠነከረበት ሁኔታም የወያኔ ደጋፊዎች የሆኑና የነበሩ የመገለባበጥ ጭላንጭል እያሳዩ መጥተዋል፤ የሰብአዊ መብት እንደማይከበር፣ አምባገነንነት እንደተንሰራፋ፣ የሕዝቡ ኑሮ እንዳልተሻሻለ፣ሙስና ጣራ እንደደረሰ፣ ተቃዋሚ አሸባሪ ተብሎ መቀመቅ እንደሚገባ በግልጽ በመመስከር ላይ ናቸው።

በመላ አገሪቱ የሕዝቡ ምሬት እየወጣ ነው። የለውጥ አየር ይነፍሳል። ድህነቱ፣ የኑሮ ውድነቱ፣ መፈናቀሉ፣ በአገሩ ባዳና ባይተዋር መሆኑ፣ተወልዶ የኖረበት ቤትና ቀዬ ተነጥቆ መሸጥ መቸብቸቡ፣ እንዳይናገር መታፈኑ፣ እንዳይሰበሰብ መታገዱ፣ ስራ አጥነቱ...ወዘተ የለውጡን ንፋስ ከሚያርገበግቡት ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህን ጥቃቶች ሆን ብሎ መመሪያ ያደረገው ስርዓት እንዲወገድለት እንጂ መልኩን ቀይሮ ወይም በተመሳሳይ ሌላ ተተክቶ እንዲቀጥል የሚሻ ዜጋ የለም።የስርዓቱ ደጋፊዎችም ቢሆኑ አብረውት አያመሹም፤ ከመጣው ጋር ለመሰለፍ ዓይናቸውን እንደማያሹ በታሪክ ተደጋግሞ ታይቷል። አሁን የሚያስፈልገው ተቃዋሚው ሃይል በአገራዊ ጉዳይ ተባብሮ በመሬት ላይ ያለውን የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎት በማጤን ሁኔታውን ተጠቅሞ የሚጠበቅበትን የታሪክ አደራና ሃላፊነት በሚገባ መወጣት ነው። ለአለው ስርዓት ወይም፣ ለተመሳሳይ ዘረኞች ስብስብ ወይም ለሌላ ነጠላ ድርጅት ዕድልና በር መክፈት አይኖርባቸውም። ሕዝቡም ምንም እንኳን ለውጥ ቢሻም በለውጥ ስም በአገሩ ጠላቶች የታጀበ ሌላ ተቀያሪ አምባገነንና የዘረኞች ስብስብ ስርዓት እንዳይመጣበት አምሮ ይቃወማል።

የአንድነት ሃይሎችና አገር ወዳዶች ይህ አደጋ እንዳይከሰት በርትተው መስራት ይኖርባቸዋል።”የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” ከሚለው የተሳሳተና አጥፊ አመለካከት መራቅ አለባቸው።ትግላቸውን ለማጠናከርና ለድል ለመብቃት በሚከተሉት ተግባራት ላይ ቢያተኩሩ የሚሻል ይሆናል።

ከሁሉ መጀመሪያ በሽግግር መንግስት አስፈላጊነት ላይ የጠራ አቋም መያዝና እንደ ግብ (ስትራተጂ) መውሰድ፣የሕዝቡንም ስነልቦና በዚያ ማነጽና ማደራጀት።

በግልጽና በድብቅ ከዳር እስከዳር ሕዝቡን ለመድረስ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች ቅስቀሳ ማድረግ፤ በተለይም በመለዮ ለባሹና በደህንነቱ ተቋም የተሰለፉት ወገኖች የአለው ስርዓት ለሚፈጽመው አገር አጥፊ ስራና ጸረ ሕዝብ እርምጃ እነሱን ተገን በማድረግ እንደሆነ እየገለጹ ከዚያ እንዲርቁና ለተሰለፉበት ሙያና አላፊነት ማለትም ለአገራዊ አንድነት፣ ነጻነትና ሰላም ተግባር እንዲያተኩሩ ማድረግ።

በውጭ አገር የሚኖረውም ለውጥ ፈላጊ አገር ቤት ካሉት እውነተኛ ለውጥ ፈላጊዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊያደርግ ይገባዋል። የሚኖርበት አካባቢ በነጻ ለመንቀሳቀስ የሚያስችለውና የኤኮኖሚ አቅሙም የተሻለ ስለሆነ በህብረት ድምጹን ማሰማት፣ በአገር ውስጥ ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለአገር አንድነት ለሚታገሉ ድርጅቶች ድጋፍና የሚያስፈልገውን የገንዘብ እርዳታ ማድረግ አለበት። በተገኘው የዜናና የግንኙነት መስመር የአገርቤቱን ትግል ማስተጋባት፣ ሰልፍ መውጣት ሊሰራቸው ከሚገባቸው መካከል ዋናዎቹ ናቸው። መንግስት ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠረው የምርጫ ሂደት ለውጥ ይመጣል ብሎ መጠበቅ የመንግስትን ጸባይና ዓላማ አለማወቅ ነው። ትግሉም ካለው ስርዓት ጋር ስልጣን ተጋርቶ ለመኖር ሳይሆን አፋኝ፣ ጎጠኛና ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነውን ስርዓት አሶግዶ በተሻለ፣የሰብአዊና የዜጋ መብትን በሚያከብር፣ ዴሞክራሲያዊና፣ ለሕግ የተገዛ፣ አገር ወዳድ ስርዓት ለማስፈን መሆን አለበት።

Website: http://www.ethioshengo.org

Email : shengo.derbiaber@gmail.com
Shengo.pr@ethioshengo.org

Tele: 44 793 760 0756
1 916 848 6790